# ደንብ

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
(MCPS)

*ተዛማጅ ሠነዶች፡-* ACH, ACH-RA, ACI, ACI-RA, COF-RA, EEB-RA, GAA, GDB-RB, IGN, JHC, JHC-RA

*ኃላፊነት የሚመለከተው ክፍል፡-* Division of Human Resources and Talent Management

## Employee Assistance Program

**I. ዓላማ**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ GAA *የሥራ ግብረኃይል ልህቀት* ላይ በተገለጸው መሠረት፣ አሁን በጡረታ ላይ ለሚገኙ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች እና ጎልማሳ የቅርብ ቤተሰብ አባሎቻቸው ሚስጥራዊ እና በፈቃደኝነት የሚተገበር  የሰራተኞች ድጋፍ ፕሮግራምን (EAP) ተግባራዊ ለማድረግ።

**II. ዳራ**

MCPS EAP ለሠራተኞች የሚሰጥ ሚስጥራዊ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የስራ ቦታ ፕሮግራም ሲሆን ይህም የሰራተኞችን ደህንነት እና ውጤታማነት ሊያደናቅፉ የሚችሉ የግል እና ድርጅታዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚያስችል ፕሮግራም ነው።

ከቦርድ ፖሊሲ GAA *የሥራ ግብረኃይል የላቀ ችሎታጋር* በሚስማማ መልኩ፣ EAP የሠራተኞችን ደህንነት ያሳድጋል እንዲሁም የድርጅቱን ተቋማዊ ጽናትን ያበረታታል፣ የሥራ ግብረኃይል ትብብርን ያዳብራል፣ የሥራ አካባቢን አውድ ለማሻሻል ስልቶችን ይቀይሳል፣ አስፈላጊ ከሆነም በስራ ቦታ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ አከራካሪ ስጋቶችን በፍጥነት እና ውጤታማ በሆነ ጣልቃ ገብነት ይፈታል።

EAP የስራ ቦታ ስጋቶችን፣ አካላዊ ህመምን፣ የአእምሮ እና/ወይም ማህበራዊ-ስሜታዊ ጉዳዮችን እና/ወይም አልኮል ወይም ሌሎች እጾችን መጠቀም የሚያስከትሉ ጉዳቶችን መፍትሔ ለማግኘት እንዲችሉ ለመርዳት የምርመራ፣ ካውንስሊንግ፣ እና የሪፈራል አገልግሎቶችን ይሰጣል።

**III. የአፈጻጸም ሒደት**

A. ሚስጥራዊነት

1. EAP በፌዴራል እና በስቴት ህጎች፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች እና በሙያዊ የስነ-ምግባር ድንጋጌዎች መሰረት የደንበኞችን ሚስጥራዊነት ይጠብቃል። EAP ሰራተኞች የደንበኛን መረጃ የሚገልጹት ከታች ያለውን ሚስጥራዊነት ከሚገድቡ ሁኔታዎች በስተቀር ከደንበኛው የጽሑፍ ፈቃድ ሲገኝ ብቻ ነው። EAP ሚስጥራዊነትን የሚገድቡ ሁኔታዎችን ለደንበኞቹ ያሳውቃል፡-

   a) በሕግ የተፈቀደላቸው ዘጋቢዎች እንደመሆናቸው፣ EAP ሰራተኞች በሕጉ መሠረት ስለ ሕፃናት ጥቃት ወይም ቸልተኝነት እንዲሁም ተጋላጭ የሆኑ ጎልማሶችን ቸልተኝነት፣ በደል ወይም ብዝበዛ በተመለከተ ጥርጣሬዎችን ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

   b) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ወይም ኮንትራክተር ለራሳቸው ወይም ለሌሎች አደጋ እንደሚያስከትል ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖራቸው የሚደርስ ጉዳትን ለመከላከል እንዲቻል EAP ሰራተኞች የደንበኛን መረጃ ይፋ ማድረግ አለባቸው።

2. ሰራተኞች EAP ውስጥ የሚሳተፉበት ሪከርድ ማለትም የህክምና ሪከርዶች ጥብቅ ሚስጥራዊ በሆነ መልኩ፣ ከሰራተኛ የግል ማህደር በተለይ በሚመለከታቸው ህጎች እና ሙያዊ የስነምግባር ድንጋጌ መሰረት በጥንቃቄ መቀመጥ አለባቸው። እነዚህን ፋይሎች እና በውስጣቸው ያሉትን መረጃዎች ለማግኘት EAP ሰራተኞች ብቻ ተደራሽነት ይኖራቸዋል።

   a) ከደንበኛው(ዋ) የጽሑፍ ፈቃድ ሳያስፈልግ MCPS የሚያገኘው ብቸኛው መረጃ ለፕሮግራም ግምገማ ዓላማ የሚሰበሰብ ስም-አልባ መረጃ ሲሆን ይህም የግል ወይም የመለያ መረጃዎችን አያካትትም። የተወሰኑ መረጃዎች የግለሰቦችን ማንነት ለመለየት የሚያስችሉ ከሆነ፣ EAP እነዚህን መረጃዎች ተቋቋሙ ባለው የአፈጻጸም ሂደት መሠረት ሪፖርት አያደርግም።

   b) EAP በካውንስሊንግ አገልግሎት የሚሳተፉ ደንበኞች ሚስጥራዊነት የሚገደብበትን የመግባቢያ መግለጫ እንዲያነቡ እና እንዲፈርሙ ይጠይቃል። EAP ጋር የመጀመሪያ ግንኙነት የጀመሩ ደንበኞች ቀውስ

በተከስተበት ጊዜ ወይም የተባባሰ ሁኔታ ወቅት ስለ ሚስጥራዊነት ገደቦች EAP ሰራተኛ በቃል ይነገሯቸዋል።

c) EAP ደንበኞች ሰራተኞች ደንበኛው(ዋ) EAP ውስጥ ያለውን/ያላትን ተሳትፎ በሚመለከት ከሌላ ሰው ጋር እንዲነጋገሩ እና/ወይም መረጃ ማግኘት እንዲችሉ የመረጃ መግለጫ ቅጽ መፈረም ይችላሉ። ይህ የደንበኛው(ዋ)ን የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሱፐርቫይዘር፣ የሥራ ግብረኃይል እና ክህሎት አስተዳደር ክፍል (DHRTM)/የሥነ ሥርአት ማስከበር እና ምርመራ ክፍል (DCI)፣ የደንበኛውን የሰራተኛ ማህበር ወይም የደንበኛውን የውጪ የህክምና አገልግሎት ሰጪ ሊያካትት ይችላል፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተገደበ አይደለም።

d) ከደንበኛ የጽሑፍ ጥያቄ ሲደርሳቸው፣ EAP ሰራተኞች የደንበኛ ሪከርዳቸውን ይፋ ማድረግ ይችላሉ። EAP ስለግላዊ መረጃ መለቀቅ ተገቢ ያልሆነ እና/ወይም EAP ደንበኛውን ጎጂ ሊሆን የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ለደንበኛው(ዋ) ያሳውቃል፣ እንዲሁም ሙያዊ ስነምግባር ላይ በመመስረት ስለሚለቀቀው ግላዊ መረጃ ሊገድብ ይችላል። ከደንበኛው(ዋ) ስለ ግላዊ ሪከርድ ለቀረበው ጥያቄ EAP ሰራተኞች 10 የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል።

B. EAP ቀጥተኛ አገልግሎቶች

1. የምርመራ እና የአጭር ጊዜ የካውንስሊንግ አገልግሎቶች

a) ደንበኞች በዓመት እስከ ስምንት የአጭር ጊዜ የካውንስሊንግ ክፍለ ጊዜዎችን በቀጥታ ከ EAP ሰራተኞች ማግኘት ይችላሉ። EAP ሰራተኞች የደንበኛን ደህንነት የሚመለከቱ የተለያዩ ተግዳሮቶችን መገምገም እና ተገቢውን የሕክምና ወይም የድጋፍ እቅድ ማዘጋጀት አለባቸው።

b) ጉዳዩ EAP ከሚያበረክተው የአገልግሎት ገደብ ውጭ ከሆነ ወይም ከሌላ ወገን ተጨማሪ ድጋፍ የሚፈልግ ከሆነ የሕክምና ዕቅዱ ተዛማጅነት

ወዳለው ተገቢ ወደሆነ MCPS ወይም የማህበረሰብ ሪሶርስ ማስተላለፍን/ሪፈራልን ሊያካትት ይችላል።

c) EAP ሰራተኞች ስለ ደንበኞች ቀጣይ የድጋፍ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑት ሪፈራሎችን ይከታተላሉ።

2. የቀውስ ጊዜ ምላሽ/ጣልቃ ገብነት

a) የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የቀውስ ክስተት ምላሽ ቡድን በትምህርት ስርዓት ውስጥ ከባድ ክስተት ሲፈጠር (ለምሳሌ፦ የተማሪ ወይም የሰራተኛ ሞት) EAP ማካተትን በሚመለከት የተደነገጉ ፕሮቶኮሎችን ይከተላል።

b) ቀውሱ በሠራተኞች ላይ ሊደርስ የሚችል ተጽዕኖ እስከፈጠረ ድረስ፣ EAP ሠራተኞች ቀውሱ በሠራተኞች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ በመገምገም ለአብዛኛዎቹ ተገቢ የሠራተኞች ድጋፍ ምክሮችን ይሰጣሉ፣ እና ለሠራተኞች ድጋፍ አቅርቦት በቀውስ ጊዜ ምላሽ ሰጪ ቡድን ውስጥ የአመራር ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።

c) EAP በስራ ቦታ ላይ የሚከሰቱ ቀውሶችን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል፣ ስለ EAP ተደራሽነት ጭምር ለ MCPS አመራር ኮንሰልቴሽን እና ስልጠና ይሰጣል።

3. ስለ ሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአመራር ስልጠና፣ ኮንሰልቴሽን፣ እና ማሠልጠን/ማዘጋጀት

a) EAP ሠራተኛ –

1) የሱፐርቫይዘሮችን የአመራር ክህሎት ለማሳደግ፣ የደህንነት ቁመናን ለማሻሻል፣ የሰራተኞችን የሥራ አፈፃፀም ብቃት ለመደገፍ እና ለሁሉም ሰራተኞች ስለ EAP አገልግሎቶች እውቀት ለማሳደግ ለሱፐርቫይዘሮች ሙያዊ ትምህርት፣ ስልጠና፣ እና የሪፈራል ፕሮቶኮሎችን ጨምሮ የኮንሰልቴሽን አገልግሎት መስጠት፣እና

2) የሥራ አካባቢን ለማሻሻል፣ ድርጅታዊ ጉዳዮችን ወይም የሠራተኞችን ደህንነት ሊነኩ የሚችሉ እና ድርጅታዊ ጽናትን ሊያሳድጉ የሚችሉ የስርዓት ለውጦችን ጨምሮ፣ መመሪያ ለሚያስፈልጋቸው የድርጅታዊ ባለድርሻ አካላት ማማከር እና ግብዓት መስጠት።

b) ከሱፐርቫይዘርነት ኃላፊነቶቻቸው ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሱፐርቫይዘሮች የሚሰጡ የምክክር እና የስልጠና ክፍለ ጊዜዎች ብዛት ገደብ አይኖራቸውም።

4. የትምህርት እና የማስተዋወቅ አገልግሎቶች

a) ለአዳዲስ ሰራተኞች ገለጻ በሚደረግበት ወቅት፣ ሁሉም አዲስ የተቀጠሩ ሰራተኞች ስለ EAP ፕሮግራም አጠቃላይ እይታ እና የሰራተኞችን ደህንነት ስለማበልፀግ እና ስለ ድርጅታዊ ጽናት ሙያዊ ትምህርት ያገኛሉ።

b) EAP ሰራተኞች ለሁሉም ሰራተኞች የማስተዋወቂያ ቁሳቁሶችን ያዘጋጃሉ፣ እንዲሁም EAP አጠቃቀምን ለማበረታታት እና የሰራተኞችን ደህንነት በሚነኩ ጉዳዮች ላይ መረጃ ለመስጠት በሚደረጉ የማስተዋወቂያ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።

5. የክርክር አፈታት ፕሮግራም

EAP ሰራተኞች ለሁሉም ሰራተኞች ያለምንም ወጪ፣ በፈቃደኝነት እና ሚስጥራዊ የገላጋይነት አገልግሎት በመስጠት የክርክር መፍቻ ፕሮግራሙን ይመራሉ፣ ይህም MCPS ጠንካራ፣ ውጤታማ የሥራ ግብረኃይል እና የመከባበር ባህልን ለማዳበር ካለው ቁርጠኝነት አንፃር ነው።

C. ሪፈራል

1. አጠቃላይ

a) EAP ውስጥ መሳተፍ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። ማንኛውም ስጋት ያለበት ሠራተኛ በፈቃደኝነት እርዳታ እንዲጠይቅ ይበረታታል። EAP የግል ሪፈራሎችን እንዲሁም ከሚመለከተው የቤተሰብ አባል፣ ጓደኛ፣ የስራ ባልደረባ፣ ወይም የሰራተኛ ማህበር ተወካይ የሚቀርቡ ሪፈራሎችን ያበረታታል።

b) የአንድ ሠራተኛ የሥራ ሁኔታ፣ እድገት፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ጥቅም በሪፈራል ወይም ወይም በግል ተነሳሽነት EAP ውስጥ በመሳተፍ ወይም ባለመሳተፍ ምክንያት አሉታዊ ተጽዕኖ አይኖረውም።

2. ሱፐርቫይዘር

EAP ሰራተኞች በየዓመቱ MCPS EAP ድረ ገጽ ላይ *የሰራተኛ ድጋፍ ፕሮግራም መመሪያ/ሃንድቡክ* አጠቃቀም መመሪያን ያሻሽላሉ። ሱፐርቫይዘሮች መመሪያውን እንዲገመግሙ እና መደበኛ የመረጃ ተደራሽነት ሂደቶችን መመሪያዎች እንዲከተሉ ይበረታታሉ።

D. የፕሮግራም ወጪ

1. በቀጥታ EAP ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ደንበኞ ምንም ወጪ አይከፍሉም።

2. በባለሙያ የሚመከር ሕክምናን በተመለከተ የሚከፈል ማንኛውም ወጪ የደንበኛው ኃላፊነት ነው። EAP ሰራተኞች በተቻለ መጠን በሠራተኛው(ዋ) የጤና እቅድ ወደሚሸፈኑ አገልግሎቶች ያስተላልፋሉ።

3. የፕሮግራሙ አገልግሎቶች ለሁሉም MCPS ሰራተኞች፣ ለጎልማሳ የቤተሰብ አባላት፣ እና ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጡረተኞች ይሰጣሉ።

E. የእረፍት ጊዜ አጠቃቀም

1. አንድ ሱፐርቫይዘር EAP እንዲጠቀም ሠራተኛን ሲያበረታታ፣ ሱፐርቫይዘሩ በስራ ሰዓት ውስጥ EAP አገልግሎቶችን ለመጠቀም ወይም ዓመታዊ ወይም የህመም ፈቃድ ለመጠቀም አመቺውን ጊዜ እንዲፈቅድ ይበረታታል።

2. አንድ ሠራተኛ በተናጥል EAP አገልግሎት ለማግኘት ከፈለገ(ች)፣ ሠራተኛው(ዋ) ከስራ ውጪ የሚሆንበትን/የምትሆንበትን ሰዓት (ይህም የዕለት ተዕለት ነፃ የምሳ ጊዜን ሊያካትት ይችላል) መጠቀም ወይም በስራ ሰዓት ውስጥ አስቀድሞ ፈቃድ መጠየቅ አለበ(ባ)ት። አንድ ሠራተኛ የእረፍት ፈቃድ ሲጠይቅ/ስትጠይቅ EAP እርዳታ ስለሚያስፈልገው/ስለሚያስፈልጋት መሆኑን ለሱፐርቫይዘሩ(ሯ) መግለጽ አይጠበቅበ(ባ)ትም።

   a) በቀጥታ MCPS EAP የሚሰጡት አብዛኛዎቹ አገልግሎቶች MCPS በህመም ፈቃድ ወይም በቤተሰብ ህመም ፈቃድ የሚከናወኑ ናቸው።

   b) EAP በግለሰብ ደረጃ ስለ እረፍት ፈቃድ ሁኔታ መመሪያ ይሰጣል፣ ወይም አንድ ሠራተኛ ከሠራተኛ ማኅበሩ ማብራሪያ መጠየቅ ይችላል።

F. MCPS የአልኮል እና ሌሎች የአደንዛዥ እፅ መድኃኒቶች ምርመራ ፕሮግራም

1. የንግድ መንጃ ፈቃድ (CDL) ያላቸው

   a) በራሳቸው ተነሳሽነት ለሚመጡ/Self-referral

      1) ከአደንዛዥ ዕፅ ወይም ከአልኮል አወሳሰድ ጋር የተያያዘ ችግር እንዳለባቸው የተገነዘቡ (CDLs) መንጃ ፍቃድ ያላቸው

በራሳቸው ተነሳሽነት EAP ማጣሪያ ግምገማ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

2) EAP ሰራተኞች ከሠራተኛው(ዋ) ጋር ተገናኝተው የችግሩን ክብደት እና የሕክምናውን አስፈላጊነት ይገመግማሉ።

3) የሠራተኛው(ዋ) የአልኮል ወይም ሌላ የአደንዛዥ ዕፅ አላግባብ መጠቀም በሌሎች ሠራተኞች ላይ አደጋ የሚያደርስ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ ካላቸው (EAP) በሙያዊ ግምገማ ካረጋገጡ ወዲያውኑ ለአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ DCI ማሳወቅ አለባቸው።

4) CDL መንጃ ፍቃድ ያላቸው ግለሰቦች ከአልኮል ወይም ከሌሎች የአደንዛዥ እፅ መድኃኒቶች አጠቃቀም ጋር ችግር እንዳለባቸው ከተረጋገጠ፣ EAP ሠራተኛው(ዋ)ን ወደ ተገቢው የሕክምና አገልግሎት ሰጪ ያስተላልፋል እና DHRTM ጋር በመተባበር ሠራተኛው(ዋ)ን ለደህንነት አስጊ ከሆነበት ቦታ ያስወግዳል።

b) MCPS ደንብ EEB-RA፣ ስለ *MCPS አውቶቡሶች ኦፕሬሽን እና ጥንቃቄ* በተገለፀው መሠረት፣ ሁሉም CDL ያላቸው አሽከርካሪዎች በዘፈቀደ፣ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖር፣ እና ከአደጋ በኋላ የአልኮል እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ ምርመራዎችን ለማድረግ ምንም እንኳን እንደዚህ አይነት ተሽከርካሪዎችን አልፎ አልፎ ብቻ የሚያሽከረክሩ ቢሆኑም ለፌዴራል እና ለስቴት መስፈርቶች ተገዢ ናቸው። በሜሪላንድ ሕግ EEB-RA ደንብ ውስጥ በተገለጹት የተወሰኑ ሁኔታዎች ድንጋጌ መሠረት የአውቶቡስ አሽከርካሪዎች በሥራ ላይ እያሉ በሕግ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮችን መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።

2. ሠራተኞች በዘፈቀደ ወይም ምክንያታዊ በሆነ ጥርጣሬ የአልኮል ወይም የሌላ ዕጽ ተጠቃሚ መሆናቸው በምርመራ ከተገኘ በፈቃደኝነት DCI በሚሰጣቸው EAP አገልግሎቶች ላይ እንዲሳተፉ ይላካሉ። EAP እና DCI ሰራተኞች ስለ ህክምናው መግባባት የሚያስችላቸውን የመረጃ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ሰራተኞች ማረጋገጫ መስጠት ይችላሉ።

G. የፕሮግራም ግምገማ

1. EAP የሚሰጣቸውን ሁሉንም አውደ ጥናቶች እና የሙያ ትምህርት ግምገማ ያደርጋል፤ እንዲሁም በአገልግሎቱ እርካታን እና በስራ አፈጻጸም ላይ ስላለው ተጽእኖ የተገኘውን ግንዛቤ ለመገምገም EAP የሚሰጠው አገልግሎት ምን ያህል እርካታ እንደሰጠ ለመገምገም ለሁሉም ደንበኞች የዳሰሳ ጥናቶችን ያቀርባል።

2. EAP ሰራተኞች የአጠቃቀም አድማሱን፣ የደንበኞችን ስብጥር፣ እና የፕሮግራሙን አፈጻጸም ለመገምገም እና ለመለካት የሚያስፈልጉ ሌሎች መረጃዎችን ይከታተላሉ።

*ስለ ደንቡ ታሪክ፦* አዲስ ደንብ ዲሰምበር 20, 2007፤ ኖቨምበር 21, 2011 ተሻሽሏል፤ ኦክቶበር 13, 2025 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፦ "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፦

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜጎች መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኸውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፦

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ኦክቶበር 2025